# የገና ጾም (ጾመ ነቢያት)

አዘጋጅ:- ፅማድ ዘክርስቶስ/ገ/እግዚአብሔር

❖ ጾመ ነቢያት (የገና ጾም) ከሰባቱ የአዋጅ አጽዋማት መካከል አንዱ ሲሆን ጾመ ነቢያት የተባለበት ምክንያት ነቢያት ስለጾሙት ነው፡፡ ነቢያት የጾሙት ስለምንድን ነው? ቢሉ ለአዳም የተሰጠውን አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ የሚለውን የተስፋ ቃል በማሰብ ከሰማየ ሰማያት ይወርዳል፣ ከድንግል ማርያም ይወለዳል፣ በሞቱም ሞት የተፈረደበትን የሰው ልጅ ነፃ ያወጣዋል ብለው ነው፡፡ እግዚአብሔር አምላክ ወልድ ሁለት ልደት አለው፡፡

አብ፡ ሰማያዊ፤

ወይነ-በቋዒ፡ ልደት፥ እንዘ-ኢይጥዕም፡ ቅድመ፣

ጽዋዐ-ልደት፥ ለወልዱ፡ ደገመ፣

ወልድሰ፡ ጽኑዕ፥ ድኅረ-ኰነነ፡ ዓለመ፣

እንዘ-በልደት፡ ይበልዕ፥ ሥጋ፡ ጥዑመ፣

ለአቡሁ፤ ኢያትረፈ፡ ዐፅመ፡፡

❖ ቀዳማዊ ልደቱ ዓለም ሳይፈጠር አካል ዘእም አካል፣ ባህሪ ዘእም ባህሪ ያለ እናት ከአብ የተወለደው ነው፡፡ መዝ 109፥3 "ቀዳማዊ በኃይል ቀን በቅዱሳን ብርሃን ከአንተ ጋር ነበር ከአጥቢያ ኮከብ አስቀድሞ አስቀድሞ ከሆድ ወለድኹህ፡፡" ድህረ አለም ከእመብርሃን ያለ አባት የተወለደው ነው፡፡ ይህን ልደት ለማክበር አስቅድመን የምንጾመው ጾም ጾመ ገና ወይም ጾመ ነቢያት ይባላል፡፡

## ይህንን ጾም የትኞቹ ነቢያት ናቸው የጾሙት?

❖ ሊቀ ነቢያት ሙሴ 40 ቀን ጾሟል ዘፀ 34፥27 ነቢዩ ኤልያስም 40 ቀን ጾሟል 1ኛ ነገ 19፥1 በተጨማሪም በተለያየ ዘመን የነበሩት ነቢዩ ዕዝራ፣ ነቢዩ ነህምያ፣ ነቢዩ ዳንኤል እንዲሁም ክቡር ዳዊት ጾመዋል፡፡

## ነቢያት ይወርዳል ይወለዳል ብለው ከጾሙ፤ እኛ እርሱ ወርዶ፣ ተወልዶ ተሰቅሎ ካዳነን በኋላ ያለን የሐዲስ ኪዳን ክርስትያኖች ስለምን የነቢያትን ጾም እንጾማለን?

❖ እኛ የነቢያትን ጾም የምንጾመው እንደቀደሙት ነቢያት ይወርዳል ይወለዳል እያልን ሳይሆን የቀደሙት ነቢያት ይወርዳል ይወለዳል እያሉ የጾሙትን በማሰብ በመጾማችን ድኅነተ ሥጋ፣ ድኅነተ ነፍስ፣ በረከተ ሥጋ፣ በረከተ ነፍስ እንድናገኝበት ነው፡፡ ጾሙ ከኅዳር እኩሌታ ጀምሮ የሚጾም ሲሆን ፍጻሜው ታህሳስ 29 በልደት በዓል ነው በዘመነ ዮሐንስ ግን ታህሳስ 28 የልደት በዓል ይከበራል፡፡

## በዘመነ ዮሓንስ በዓለ ልደት በታህሳስ 28 መከበሩ ስለምንድን ነው?

❖ የምሥጢረ ሥጋዌ ዋናው ትምህርት ምሥጢረ ተዋሕዶ ነው ይህን የማኅፀኑን ምሥጢር ቍጥሩን ለመጠበቅ ነው፡፡ መጋቢት29 ቀን ቃል ሥጋ የሆነበትና በድንግል

ማኅፀን የተፀነሰበት ዕለት ነው፡፡ ከዚህ ከመጋቢት 29 ቀን ጀምሮ ወንድ ልጅ በእናቱ ማኅፀን የሚቆይባቸውን ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀናት ስንቆጥር ጳጉሜን ጨምሮ ዕለተ ልደቱ ታኅሣሥ 29 ቀን ላይ ይውላል፡፡ አደማመሩን ከተመለከትን

- ከመጋቢት 29 ጀምሮ እስከ ነሐሴ 30 ድረስ 151 ዕለት ይሆናል፣
- ጳጉሜ 5 ዕለት፣ ከመስከረም እስከ ታህሳስ 29 ድረስ 119 ዕለት ነው
- ኣንድ ላይ ስንደምረው 151+ 5 + 119= 275 (275 ማለት 9 ወር ከኣምስት ቀን ማለት ነው) ይህ ስሌት በዘመነ ማቴዎስ፣ በዘመነ ማርቆስ እና በዘመነ ሉቃስ ሲሆን ነው፡፡

❖ ስለዚህም መጋቢት 29 ቀን የተፀነሰው ጌታችን ከኃጢአት በቀር የሰውነትን ሥራ ሁሉ ፈጽሟልና ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን በእናቱ ማኅፀን ቆይቶ ታኅሣሥ 29 ቀን በቤተልሔም ዘይሁዳ ተወለደ፡፡

❖ በዘመነ ዮሐንስ ግን በ 3 ዓመት ማለትም በሉቃስ ዘመን ጳጉሜን 6 ስለምትሆን ለቀጣዩ ዓመት ማለትም በዮሐንስ ዘመን ልደት ታኅሳስ 28 ይሆናል ፡፡ በዘመነ ዮሐንስ ታኅሣሥ 28 የሆነበት ምክንያት ዘመነ ሉቃስ ጳጉሜን 6 ስለሚሆን ጌታ ደግሞ የተፀነሰው መጋቢት 29 ቀን ነው ከዚያ ከመጋቢት 29 ጀምሮ ያሉትን ቀናት ብንቆጥር እስከ ታኅሣሥ 28 ቀን 275 ቀን 9 ወር ከ 5 ቀን ስለሚሆን ነው፡፡ አደማመሩን ከተመለከትን

- ከመጋቢት 29 ጀምሮ እስከ ነሓሴ 30 ድረስ 151 ዕለት ይሆናል
- ጳጉሜን 6 ዕለት፣ ከመስከረም እስከ ታህሳስ 28 ድረስ 118 ዕለት ነው
- ኣንድ ላይ ስንደምረው 151+ 6 + 118= 275 275 ማለት 9 ወር ከ5 ቀን ማለት ነው፡፡

❖ እስከ ታህሳስ 29 ግን ብንቆጥረው 276 9 ወር ከ6 ቀን ይሆንብናል ይህም የማኅፀኑን ምሥጢር ያፋልስብናል፡፡ ሰልዚህ በሊቃውንተ ቤተክርስቲያን አስተምሕሮ የልደት በዓል የሠግር 28 ቀንና የአዘቦቱ 29 ቀን ይውላል በማለት ይገልጹታል፡፡ "ሠግር" ማለት ተሻጋሪ ዘላይ ማለት ነው፡፡ ዓመቱ 365 ቀናት መሆኑ ቀርቶ 366 ቀን ሲሆን ወይም ጳጉሜ 5 ቀናት መሆኗ ቀርቶ 6 ቀን ስትሆን ማለት ነው፡፡ ጳጉሜን በዘመነ ሉቃስ 6 ቀናት ስትሆን ዘመነ ዮሓንስ የሚጀምርበትን መስከረም 1ን በኣንድ ቀን ማዘግየቷን ነው፡፡ ኣንድ ቀን ታዘልለውና እንደሌሎቹ ዓመታት በ1 መጀመሩን ትቶ መስከረም 2 ሊሆን በሚገባው ቀን ይጀምራል፡፡ በአዘቦት ዓመታት ዘመነ ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስ መስከረም 2 ሊሆን የሚገባውን ቀን በዘመነ ዮሐንስ ግን መስከረም 1 ያደርገዋል፡፡ መስከረም አንድ በአንድ ቀን ዘግይቶ ከጀመረ ወራቱ ሁሉ ታኅሣሥን ጨምሮ ማለት ነው አንድ ቀን እያሳለፉ መጀመር ግድ ይሆንባቸዋል፡፡ ልደት ግን አብሮ አይዘገይም ማለትም 9ወር ከ5 ቀን ማለፍ ስለሌለበት ይህንን የማኅፀኑን ቊጥርን ይጠብቃል፡፡ ስለዚህ በሠግር ዓመት ቀደም ብሎ በታኅሣሥ 28 ቀን ይውላል፡፡ የሠግር 28 ቀንና የአዘቦቱ 29 ቀን ይውላል ማለታቸው ስለዚህ ነው፡፡

## በዘመነ ዮሐንስ በዓሉ በታህሳስ 28 ከሆነ የጾሙ ዕለት 43 ስለሚሆን ጾመ ጋድ አለን?

❖ በዘመነ ዮሐንስ በዓሉ በ ታህሳስ 28 ከሆነ የጾሙ ዕለት 43 ስለሚሆን ጾመ ጋድ አለን? ቢሉ አዎ አለ መኖሩም የሚታወቀው በዚህ ዘመን ልደት ታህሳስ 28 በረቡዕ እና አርብ ቢውል እንደሌሎቹ 3ቱ ዘመናት ፍስክ ሆኖ የሚበላ በመሆኑ አስረጂ ነው።

❖ በተጨማሪም የዘመነ ዮሐንስን ጾመ ጋድ በ3ቱ ዓመታት (በማቴዎስ፣ በማርቆስ፣ በሉቃስ) ጾመ ጋድ ባሉት ትርፍ ሰዓታት ጾሙን ስለምንጾም ነው። ይህ ማለት የማቴዎስ የማርቆስ የሉቃስ የልደት ጋድን ከጾም መደበኛ ሰዓት (9 ሰዓት) አትርፈን ነው የምንጾመው በዚህ የሦስቱ ዓመታት ያሉት አትርፈን የጾምናቸው ስንደምር ለዘመነ ዮሐንስ ጾመ ጋድ ይሆናሉ ማለት ነው።

## በዘመነ ዮሐንስ በዓለ ልደትን ታህሳስ 28 ማግሰኞ እና ሐሙስ ላይ አርፎ በዓሉን አክብረን ታህሳስ 29 የሚውለው ረቡዕ እና አርብ ቢሆን ይጾማልን?

❖ የልደት በዓል በየዓመቱ ታህሣሥ 29 ዕለት ሲሆን፤ በዘመነ ዮሓንስ ግን የዘመነ ሉቃስ ጳጉሜን ስድስት ዕለት ስለምትሆን ልደቱን ታህሣሥ 28 ዕለት ይከበራል። ነገር ግን በ29 የጌታችን ልደት መታሰቢያነቱ አይቀርም። ለምሳሌ በዘመነ ዮሐንስ 28 ማግሰኞ ልደቱን ቢከበር በነጋታው በ29 ረቡዕ የልደቱ መታሰቢያነት እንዳለ ሆኖ ዘመነ ዮሓንስ እና ረቡዕ ስለሆነ ግን እንጾማለን ይጾማል።

❖ ይህን ጾም በዘመነ ብሉይ እና በዘመነ ሐዲስ ብዙ ቅዱሳን ጾመውታል በቤተክርስቲያናችንም ለጾሙ ከተሰጡት ስያሜዎች እነዚህ ናቸው ፦

### 1. ጾመ አዳም

❖ ለአዳም የተነገረው ትንቢት ስለተፈጸመበት ይህንን ስያሜ አግኝቷል። አዳም ዕፀ በለስን በልቶ ከገነት ከተባረረ በኋላ በፍጥረቱ ገዢ አድርጎ በገነት ያኖረኝን ፈጣሪዬን ትቼ የፍጡሩን ቃል ሰምቼ ትዕዛዝን አፍርሼ አሳዘንኩት ብሎ በፈጸመው በደል አዝኖ ተክዞ ፣ ጾመ ፣ ጸለየ ከልብ የሆነ ጸጸቱንም እንባውን በራሱ መፍረዱንም ዓይቶ እግዚአብሔር ተስፋ ድኅነት ሰጠው በአምስት ቀን ተኩል በማለት ከአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን በኋላ ከሰማየ ሰማያት ወርጄ ከድንግል ማርያም ተወልጄ በፈቃዴ ተገፍፌ በዕለተ አርብ በመልዕልተ መስቀል ተሰቅዬ ሥጋዬን ቆርሼ ደሜን አፍስሼ ሞቼ ተነስቼ አድንሃለሁ" ብሎ ቃል ኪዳን ገባለት አዳምም ያለውን እንደ ተለመደው አቆጣጠር መስሎት እስከ ኣምስት ቀን ጠበቀ በኋላ ግን አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም በፈቃዴ ተገርፌ በዕለተ አርብ በመልዕልተ መስቀል ተሰቅዬ ሥጋዬን ቆርሼ ደሜን አፍስሼ ሞቼ ተነስቼ አድንኃለው እንዳለው ተረድቶ ይህን ተስፋ በልቡናው ተሸክሞ ይኖር ነበር። ነጋዴ ስንቁን ይዞ እየበላለት ከዚህ እስከዚያ ያደርሰኛል እያለ እንዲጓዝ በአጸደ ሥጋ በአጸደ ነፍስም ሳለ ጌታ እንዲህ ብሎኛል እና ይምረኛል እያለ ተስፋውን ኣጽንቶ ሲጠባበቅ ኖረ ለልጆቹም ሁሉ ነገረ። ትንቢት ተነገረ ሱባዬ ተቆጠረ። 5500 ዘመን ሲፈጸምም የማያደርገውን

የማይናገር የተናገረውንም የማያስቀር ጌታ ከዘመን ዘመን ከወሩ ወር ከዕለታቱ ዕለት ከሰዓቱ ሰዓት ሳይጎል በጽኑ ቀጠሮ የአዳም የልጅ ልጅ ከምትሆን ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ። ገላ 4÷4 “ወአመ በጽሐ ዕድሜሁ ፈነወ እግዚአብሔር ወልዶ ወተወልደ እምብእሲት ወገብረ በሕገ አሪት / ነገር ግን ቀጠሮ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ልጁን ላከ ከሴትም ተወለደ የኦሪትንም ሕግ ፈጸመ” እንዲል ስለዚህ ጾሙ ለአዳም የተሰጠው ተስፋ የተቆጠረው ሱባዔ ስለተፈጸመበት ጾመ አዳም ይባላል።

## 2. ጾመ ነቢያት

- ነቢያት የተናገሩት ትንቢት ስለተፈጸመበት ይህንን ስያሜ ኣግኝቷል፦ በየዘመናቱ የተነሱ ነቢያት እግዚአብሔር ወደፊት ሊያደርግ ያሰበውን በእምነት ዓይን እያዩ ምሥጢር ተገልጦላቸው የራቀው ቀርቦ የረቀቀው ገዝፎ እየተመለከቱ ትንቢት ተናገሩ፤ ያዩትን መልካም ነገር እንዲደርስላቸው ጾሙ ጸለዩ። ነቢያት ስለመወለዱ፣ ወደ ግብጽ ስለመሰደዱ፣ በባህረ ዮርዳኖስ ስለመጠመቁ ብርሃን በሆነው ትምህርተ ወንጌል ጨለማን ዓለም ስለማብራቱ ለሰው ልጆች ድኅነት ጸዋትወ መከራ ስለመቀበሉ እና ስለመስቀሉ ስለ ትንሳኤው ስለ እርገቱ እና ስለዳግም ምጽኣቱ ትንቢት ተናግረው ኣላቆሙም፤ ለአዳም የተሰጠው ተስፋ ተገልጦላቸው ለተናገሩት ትንቢት ፍጻሜ እንዲያደርሳቸው ፈጣሪኣቸውን ተማጽነዋል በየዘመናቸው “ፈኑ እዴከ እምአርያም አድኅነኒ ወባልሐኒ እማየ ብዙኅ እጅህን ከአርያም ላክ አድነኝ ከብዙ ውኃም ተቤዠኝ” መዝ 143÷7 እያሉ ጮኹ በጾምና በጸሎትም ተወስነውም ሰው የሚሆንበትን ጊዜ በቀናት፣ በሳምንታት፣ በወራት እና በዓመታት ቆጠሩ ጌታችን ከእመቤታችን ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ ሰው ሆኗል ነቢያት ተስፋው በዘመናቸው ተፈጽሞ በዓይነ ሥጋ ለማየት ባይችሉም አምነው ከወዲሁ ተደሰቱ እንዲሁም በጌታ ልደት ትንቢተ ነቢያት ስለተፈጸመበት ይህ ጾም ጾመ ነቢያት ይባላል።

## 3. ጾመ ስብከት

- የወልደ እግዚአብሔርን ሰው መሆን ያስተማሩበት አንድም በዘመነ ሐዲስ ስለ እግዚአብሔር ሰው መኾን በስፋት ትምህርተ ወንጌል የሚሰጥበት ወቅት በመኾኑም ጾመ ስብከት ይባላል።

## 4. ጾመ ልደት

- የጾሙ መጨረሻ ወይም መፍቻ በዓለ ልደት በመኾኑ ደግሞ ጾመ ልደት (የልደት ጾም) በመባል ይታወቃል።

## 5. ጾመ ሐዋርያት

- ቅዱሳን ሐዋርያት በዓለ ትንሣኤን ዐቢይ ጾምን ጾመን እናከብረዋለን፤ በዓለ ልደትንስ ምን አድርገን እናከብረዋለን? በማለት ነቢያት የጾሙትን ከልደተ ክርስቶስ በፊት ያለውን ጾም ጾመዋልና ጾመ ሐዋርያት ይባላል።

## 6. ጾመ ፊልጶስ

- ሐዋርያው ቅዱስ ፊልጶስ በአፍራቅያና አውራጃዋ ኹሉ እየተዘዋወረ በጌታችን አምላካችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስም ወንጌልን በማስተማር፣ ድንቅ ድንቅ ተአምራትን በማድረግ ብዙዎችን ወደ አሚነ እግዚአብሔር ሲመልስ ቀይቶ ትምህርቱን በማይቀበሉ የአፍራቅያ ሰዎች አማካይነት በሰማዕትነት ዐርፏል። ደቀ

መዛሙርቱ ሥጋውን ሊቀብሩ ሲሉም ስለ ተሰወረባቸው የሐዋርያውን ሥጋ ይመልስላቸው ዘንድ ሱባዔ ይዘው፣ በጾም በጸሎት ተወስነው በለመኑት ጊዜ እግዚአብሔር ልመናቸውን ተቀብሎ በ፫ኛው ቀን መልሶላቸው ሥጋውን (አስከሬኑን) በክብር አሳርፈውታል፡፡ ደቀ መዛሙርቱ የሐዋርያውን ሥጋ ካገኙ በኂላ እስከ ጌታችን ልደት ድረስ ጾመዋል፡፡ ስለዚህም ጾመ ነቢያት ጾመ ፊልጶስ እየተባለ ይጠራል፡፡

## 7. ጾመ ማርያም

❖ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም ይህን ጾም ጾማዋለች ፡፡ ይህም ቅዱስ ገብርኤል ወልደ አምላክን ያለ ሰስሎተ ድንግልና (ድንግልና ያለማጣት) በግብረ መንፈስ ቅዱስ ጸንሳ እንደምትወልደው ካበሰራት በኂላ እመቤታችን ትሁት ናትና ምን ሠርቼ እወልደዋለሁ ብላ ጌታን ከመውለዷ አስቀድሞ ጾማዋለችና ‹‹ጾመ ማርያም›› ይባላል፡፡ ይህን ጾም ነቢያት እና ሐዋርያት ጾመውት በረከት አግኝተውበታል በመሆኑም የቤተ ክርስቲያን ኣባቶች ምእመናን በመጾም እንዲጠቀሙበት ሥርዓት ሠርተዋል፡፡

### ይህ ጾም ስንት ጊዜ ነው ቢሉ?

❖ 44 ቀን ነው፡፡ 40 ዕለታት የነቢያት ጾም ሲሆን ከቀሩት ከ4ቱ ሦስቱ ዕለታት 2 ምክንያቶች በማሰብ የምንጾማቸው ናቸው፡፡

1. ስምዖን ጫማ ሰፊው (አብርሃም ሶሪያዊ) የጾሙትን ጾም ለማሰብ ነው፡፡ በአገሩ ያሉ አሕዛብ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ “ የሠናፍጭ ቅንጣት ታህል እምነት ቢኖራችሁ ይህንን ተራራ ከዚህ ተነቅለህ ወዲያ ሂድ ብትሉት እንዳላችሁት ይሆንላችኂል” ይላል እንግዲያውስ ይህንን በተግባር ያሳዩንና እኛም በእነርሱ እምነት እንመን በማለት ከአገሩ ንጉሥ ዘንድ በመቅረብ ሊቀ ጳጳሱን አብርሃምን ጠየቁት አባታችንም ሦስት ዕለታትን እንዲሰጡት ነግሯቸው ወደ እመቤታችን ሥዕል ፊት ቀርቦ ይህንን ተኣምር ታደርግለት ዘንድ ተማጸናት ተለማኝቱም ይህን ድንቅ ተአምር ይፈጸምልህ ዘንድ ምን ማድረግ እንዳለብህ የሚያስረዳህ ስምዖን የሚባል ሰው አለ ከመንገድ ዳር ተቀምጦ ጫማ ሲሰፋ ታገኘዋለህ አለችው፡፡ አባታችንም ወደ ርሱ ሄዶ የሆነውን ሁሉ ነገረው ቅዱስ ስምዖን ግን “እመቤቴ ሆይ እኔነቴን ስለምን ገለጥሽኝ በዚህ መኖሬን አልፈቀድሽውምን እንግዲያውስ ትዕዛዝሽን እፈጽማለሁ በዓቴን ግን ዕለቃለሁ” አለ ይህም ቅዱሳን ውዳሴ ከንቱን ስለማይወዱ ክብራቸው በተገለጠበት ቦታ ስለማይኖሩ ነው፡፡ በመቀጠልም ሊቀ ጳጳሱን ሦስት ቀን ያህል እንጹም ሦስተኛውም ቀን በተፈጸመ ጊዜ ህዝቡን ሰብስበህ በተራራው ሥር እግዚኦታ ታደርሳለህ ተአምሩም ይፈጸምልሃል በማለት ነገረው እንደተነገረውም ከሦስት ቀን ጾም በኂላ ሕዝቡን ሰብስቦ እግዚኦታ ሲያደርስ ቅዱስ ስምዖንም ከመካከላቸው ሆኖ “ ጌታ ሆይ የእነርሱ ክብር እንዲገለጥ ብለው አይደለም የአንተ ክብር እንዲገለጥ፥ አሕዛብም በኣንተ ያመልኩ ዘንድ ነውና እባክህን ስማቸው” እያለ ይማጸንላቸው ጀመር ተራራው ከሥሩ ተነስቶ ክርስቲያኖችን ያስቸግር የነበረውን ባሕር ደፍኖላቸዋል በዚህም አሕዛብ አምነዋል ፤ በባህሩ ምክንያት ተለያይተው የነበሩ ክርስቲያኖችም ተገናኝተዋል፡፡ ስለዚህ እንዲህ ያለ ድንቅ ተአምር የተፈጸመበት ጾም ስለሆነ ከነቢያት ጾም ጋር በአንድነት እንድንጾመው አባቶች አዘዋል፡፡

2. ሐዋርያው ቅደስ ፊልጶስ ሐዋርያት ዓለምን ዞረው ለማስተማር ዕጣ ሲያወጡ ለፊሊጶስ ከወርቅ የተሠራ አሞራ የሚያመልኩ ሰዎች ያሉበት አገር ደረሰው ገድለ ሐዋርያት ላይ አፍራቅያ ይለዋል የአገሩን ስም ቱርክ አካባቢ የሚገኝ ነው፤ ወደ ከተማው ገብቶ ወንጌለ መንግስተ ሰማያትን ሰበከ ብዙዎችንም አሳመነ አጠመቃቸው፤ አቆረባቸውም፤ ቤተክርስቲያን ሠራላቸው፤ ካህንና ዲያቆንም ሾመላቸው፤ ልቡናን የሚያስደምም ድንቅ ድንቅ ተአምራትንም አደረገ፣ ብዙዎችንም እግዚአብሔርን ወደ ማወቅ መለሰ:: ወደ ሌሎች ብዙ አገሮችም ተዘዋውሮ የከበረ የወንጌልን ቃል በማስተማር ሰዎችን ወደ ሃይማኖት ሲጠራ ኖረ ብዙዎችንም ክብር ይግባውና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አሳመነ:: ነገር ግን ጥቅማቸው የጎደለባቸው የጣኦት ካህናት ከንጉሡ ጋር ነገር ሠርተው አጣሉት ይዘው አሠሩት ጽኑዕ ሥቃይንም አሠቃዩት:: እርሱ ግን ከዘለዓለም ሕይወት ስለ ምን ትርቃላችሁ? የነፍሳችሁንስ ድኅነት ለምን አታስቡም? ይላቸው ነበር:: እነርሱም ልቡናቸው ደንድኗልና ብዙ መከራ ካጸኑበትና ካሠቃዩት በኂላ ኅዳር 18 ቀን ዘቅዝቀው ሰቀሉት፤ ነፍሱንም በእግዚአብሔር እጅ ሰጠ:: ሥጋውን በእሳት ሊያቃጥሉት በወደዱ ጊዜ ከእግዚአብሔር የተላከ መልአክ ከእጆቻቸው መካከል ነጠቃቸው እያዩትም ወስዶ ሠወረው:: ይህንንም ተመክተው ስለገደሉት ተጸጽተው ያዘኑና ያመኑ ብዙዎች ቢጾሙና ቢጸልዩ ቢለምኑ ሰውን የሚወድ ቸር ይቅር ባይ ጌታችን ልመናቸውን ተቀብሎ በ3 ቀን መልሶላቸው በፍጹም ደስታ አሳረፉት:: ይህን ያዩ ሁሉ ወደ እምነቱ ገቡ:: ከሐዋርያው ፊልጶስም ሥጋ ታላላቅ የሆኑ ድንቅ ድንቅ ተኣምራት ተገልጠዋል:: ደቀ መዛሙርቱ ግን ጾሙን ጀምረን አንተወውም ብለው እስከ ልደት በዓል ድረስ ጾመውታል:: ስለዚህ ነገርም ጾመ ፊልጶስ ይባላል:: ቁጥሩም 43 ይሆናል፡፡ 44ተኛ ሁና የምትቆጠረው ጾመ ጋድ(ገሐድ) ናት::

❖ የነቢያት ጾም የሚጀምረው ዘመነ አስተምሕሮ በገባ በሁለተኛው ሳምንት ማለትም በቅድስት ሰንበት ነው:: ዘመነ አስተምህሮ ምንድን ነው ቢሉ?

❖ ይህ ዘመነ አስተምህሮ ወቅቱ ወይም ጊዜው ከኅዳር 6 ጀምሮ እስከ ታኅሣሥ 7 ወይም 13 ቀን ድረስ ያለው ወቅት ዘመነ አስተምሕሮ (አስተምህሮ) ይባላል፡፡

➢ **አስተምህሮ** ቃሉ በሃሌታው “ሀ” (“አስተምህሮ” ተብሎ) ሲጻፍ የቃለ እግዚአብሔር ማስተማሪያ ማለትም የትምህርተ ወንጌል ዘመን ማለት ነው:: ሥርወ ቃሉም “መሀረ--አስተማረ፤ ለመምህር ሰጠ፤ መራ፤ አሳየ፤ መከረ፤ አለመደ” ወይም “ተምሀረ--ተማረ፤ ለመደ” የሚለው የግእዝ ግስ ሲሆን፣ ይኸውም የእግዚአብሔር ቸርነቱ፣ ርኅራኄው፣ ትዕግሥቱና የማዳን ሥራው በቤተክርስቲያን በስፋት የሚሰበክበት ጊዜ ነው፡፡

➢ **አስተምሕሮ** ቃሉ በሐመሩ “ሐ” (“አስተምሕሮ” ተብሎ) ሲጻፍ ደግሞ የምሕረት፣ የይቅርታ ዘመን ማለት ነው:: ሥርወ ቃሉም “መሐረ--ይቅር አለ፣ ዕዳ በደልን ተወ” ወይም “አምሐረ--አስማረ፤ ይቅር አሰኘ፤ አራራ፤ አሳዘነ” የሚለው የግእዝ ግስ ነው፡፡ ዘመነ አስተምሕሮ ስለ እግዚአብሔር ቸርነትና ርኅራኄ፤ እርሱ በደላችንን ሁሉ ይቅር እንደሚለን እኛ ምእመናንም እርስ በእርስ ይቅር መባባል እንደሚገባን ትምህርት የሚሰጥበት ወቅት ነው፡፡

❖ በዘመነ አስተምሕሮ የሚገኙ ሰንበታት በቅዱስ ያሬድ የዜማ መጻሕፍት እንደተቀመጠው በዘመነ አስተምሕሮ ውስጥ የሚገኙ ሰንበታት ወይም እሑዶች አራት ሲሆኑ

1. አስተምሕሮ (ኢተዘኪሮ)

❖ በዘመነ አስተምህሮ ያለው የመጀመሪያው ሰንበት አስተምህሮ ወይም ኢትዝክሮ ይባላል። ኢትዝክሮ ለምን ተባለ ቢሉ እግዚአብሔር ክቡር የሆነ የሰው ልጅ ቀርቶ ከፍጥረቶቹ መካከል አንዲቱ ፍጥረት በከንቱ እንድትጠፋ እንደማይፈልግና ታላቅ መሐሪ መሆኑን ሲያስረዳ ነው። እንዴት ቢሉ መጻሐፍ "ኢተዘኪሮ አበሳ ዚአነ ኢኀደገነ ፍጹመ ንማስን ኄር እግዚአብሔር።  በደላችንን ሳያስብ እንጠፋ ዘንድ ዘንድ ከቶ ያልተወን ቸር አምላክ ነው።" መዝ 78÷8 ይላልና የእርሱን መሐሪነት ሲያጠይቅ አንድም በዕለቱ የሚዘመረው መዝሙር ኢትዝክሮ በሎ ይጀምራልና የመጀመሪያዋ ሰንበት ኢትዝክሮ ትባላለች።

2. ቅድስት (ሎቱ ስብሐት)

❖ በዘመነ አስተምህሮ ያለው ሁለተኛው ሰንበት ቅድስት ወይም ሎቱ ስብሐት ይባላል። ሎቱ ስብሐት ለምን ተባለ ቢሉ ዓለምን በከሃሊነቱ የፈጠረ፤ ሊነገር በማይቻል መሥዋዕትነት ዓለምን ያዳነ ወልደ አብ ወልደ ማርያም ክርስቶስ እንደሆነ ሰንበትን የቀደሳት የምስጋና ቀን ያድረጋት እርሱ እንደሆነ ሲናገር ነው። እንዴት ቢሉ በመጻሐፈ መዝሙር ዘቅዱስ ያሬድ "ሎቱ ስብሐት ወሎቱ አኰቴት ለዘቀደሳ ለሰንበት አልቦ አመ ኢሀሎ ወአልቦ አመ ኢሀሎ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር ዘገብሮ ለሰብእ በአርአያ ዚአሁ ኵሉ ውስተ እዴሁ ውእቱ ይኴንን ስማያተ ወምድረ ገብረ በከመ ፈቀደ አምላክ ወልደ እግዚአብሔር። / ሰንበትን ለቀደሳት፤ ላከበራት፤ ለለያት፣ ላጸናት ለእርሱ ክብርና ምስጋና ይገባል፣ እርሱ የሌለበትና የማይኖርበት ጊዜ የለም፤ እርሱ ያልነበረበት ጊዜ አልነበረም፣ ሰውን በእርሱ አርአያና አምሳል የፈጠረው የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ ሁሉ በእጁ ውስጥ ነው፣ ሰማይንና ምድርን ይገዛል ያስተዳድራል፣ የእግዚአብሔር ልጅ እርሱ እንደ ፈቀደ ሁሉን አደረገ።" እንዲል ስለዚህም ሰንበት ቅድስት እንደሆነች ሲያጠይቅ ቅድስት ተብላለች። አንድም በዕለተ ሰንበት ለእግዚ አብሔር ምስጋና የሚቀርብባት ናትና ሎቱ ስብሐት ተብላለች። አንድም በዕለቱ የሚዘመረው መዝሙር ሲጀምር ሎቱ ስብሐት ብሎ ይጀምራልና ሁለተኛዋ ሰንበት ሎቱ ስብሐት ትባላለች።

3. ምኩራብ (አምላክ ፍጹም በሕላዌሁ)

❖ በዘመነ አስተምህሮ ያለው ሦስተኛው ሰንበት ምኩራብ ወይም አምላክ ፍጹም በሕላዌሁ ይባላል። አምላክ ፍጹም ለምን ተባለ ቢሉ በመጻሐፈ መዝሙር ዘቅዱስ ያሬድ በዕለቱ የሚዘመረው መዝሙር "አምላክ ፍጹም በህላዌሁ ዘሀሎ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም ዘበመንግሥቱ ይኴንን ዓለመ ሰማየ ገብረ ለስብሐቲሁ ዓለመ ፈጠረ ወምድረ ሣረረ ወገሠፀ ባሕረ ወገሠፆሙ ለኵሉ ፍጥረት እለ ውስተ ደይን ያዕርፉ ባቲ አብ ቀደሳ ለሰንበት ቅረቡ ኀቤሁ ለአምላከ ጽድቅ ማኅደር ለንጹሓን ከመ ትንሥኡ አክሊለ ስብሐት ዘአስተዳለወ ለእለ ያ ያፈቅርዎ ቅርዎ ጸንዑ በጸጋ በሥን ወበሃይማኖት ወረሱ አክሊለ ስምዕ በእምነቶሙ እለ እምዓለም አሥመርዎ ለእግዚኦሙ መምህረ ቅዱሳን አክሊለ ሰማዕት ሠያሜ ካህናት። / ቅድመ ዓለም በመንግሥቱ የነበረ፤ በአነዋወሩ ፍጹም አምላክ የሆነ፤ ዓለምን ይገዛል፤ ሰማይን ለክብሩ አደረገ፤ ዓለምን ፈጠረ ምድርን ሠራ አዘጋጀ፤ አበጃጀ፣ ባሕርን ገሠፀ፤

ፍጥረትን ሁሉ ገሠፃቸው፤ በመከራ ውስጥ ያሉ ያርፉባት ዘንድ እግዚአብሔር አብ ሰንበትን ቀደሳት አከበራት ከፍ ከፍ አደረጋት፤ በንጹሓን ማደሪያ ለሚወዱት ያዘጋጀውን የክብር አክሊልን ትቀዳጁ ዘንድ ወደ እውነት አምላክ ቅረቡ፤ በዓለም ሳሉ የቅዱሳን መምህራቸው፣ የሰማዕታት አክሊላቸው የካህናት ክብራቸው የሆነውን ጌታቸውን ደስ ያሰኙት ዘንድ በሃይማኖት፤ በጸጋና በልጅነት ጸኑ፤ በእምነታቸውም የምስክርነትን አክሊልን ወረሱ።" ይላልና ሲጀምር አምላክ ፍጹም ብሎ ይጀምራልና ሦስተኛዋ ሰንበት አምላክ ፍጹም ትባላለች።

## 4. መጻጉዕ (ይቤሉ እስራኤል)

- ❖ በዘመነ አስተምህሮ ያለው አራተኛው ሰንበት መጻጉዕ ወይም ይቤሉ እስራኤል ይባላል። ይቤሉ እስራኤል ለምን ተባለ ቢሉ በመጸሐፈ መዝሙር ዘቅዱስ ያሬድ በዕለቱ የሚዘመረው መዝሙር "ይቤሉ እስራኤል ኢርኢነ ወኢሰማእነ ዘዕውሩ ተወልደ ወተከሥታ አዕይንቲሁ በሰንበት ለእመ እምኀበ እግዚአብሔር ኢኮነ አመ ኢገብረ ዘንተ ወይቤልዎ ወምንተ ትብል በእንተ ዘአሕየወኒ ይቤለኒ ኢትንግር ወእምዝ ዘየአኪ ኢይርከብከ። / እስራኤል አላየንም አልሰማን አሉ፤ ዕውር ሆኖ የተወለደው በሰንበት አይኖቹ ተከፈቱ፤ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ካልሆነ በቀር ይህን ማድረግ አይቻልም አሉ፣ ስላዳነህ ምን ትላለህ? አሉት፤ ከዚህ የከፋ እንዳያገኝህ ይህን ለማንም አትናገር አለኝ አላቸው።" እንዲህ በማለት ይጀምራልና አራተኛዋ ሰንበት ይቤሉ እስራኤል ትባላለች። አንድም
- ❖ "በሰንበት ወረቀ ምድረ ወገብረ ዕቡረ አሕየወ ዕውረ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ ይትፌሥሑ ጻድቃን በብዙኀ ሰላም ሎሙኒ ፀሓየ ጽድቅ ሠረቀ ሎሙ። / ቅድመ ዓለም የነበረ ዛሬም ያለ ወደፊትም ዓለምን አሳልፎ ለዘለዓለም የሚኖር ጌታ በሰንበት ወደ ምድር ምራቁን እንትፍ ብሎ ጭቃ አደረገ የታወረውን አዳነ፤ በማዳኑም ጻድቃን ደስ ይላቸዋል፤ ለእነርሱ በብዙ ሰላም የጽድቅ ፀሓይ ወጣላቸው።" እንዲህ በማለት ይዘምራልና።

## 5. ደብረ ዘይት (ሠርዐ ሰንበተ ለሰብእ እረፍተ)

- ❖ በዘመነ አስተምህሮ ያለው አምስተኛው ሰንበት ደብረ ዘይት ወይም ሠርዐ ሰንበተ ለሰብእ እረፍተ ይባላል። ሠርዐ ሰንበተ ለሰብእ እረፍተ ለምን ተባለ ቢሉ በመጸሐፈ መዝሙር ዘቅዱስ ያሬድ በዕለቱ የሚዘመረው መዝሙር "ሠርዐ ሰንበተ ለሰብእ ዕረፍተ ለእለ በሰማይ ወለእለ በምድር ለእለ በባሕር ወለእለ በየብስ (ሠ) ለአበዊነ ነቢያት ወለሐዋርያት (ሠ) ለጻጻሳት ወለቀሳውስት ለዲያቆናት ወለመነኮሳት (ሠ) ለጻድቃን ወለኀጥአን ለሙታን ወለሕያዋን (ሠ) ሰንበተ ለሰብእ ዕረፍተ ሰንበቱሰ ለክርስቶስ ይእቲ ወማኀደረ ስሙ ለልዑል። / በሰማይ፣ በምድር፣ በባሕርና በየብስ ለሚኖር ሁሉ ለዕረፍት ሰንበትን ሠራ፤ ለአባቶቻችን ለነቢያት፣ ለሐዋርያት፣ ለጳጳሳት፣ ለቀሳውስት፤ ለዲያቆናትና ለመነኮሳት፣ ለጻድቃንም፣ ለኀጥአንም፣ ለሙታንም፣ ለሕያዋን ለሰው ሁሉ ዕረፍት እንዲኾን ሰንበትን ሠራ፤ ይኸቺውም የክርስቶስ ሰንበት ናት፣ የልዑል የስሙ ማደሪያው ናት።" ይላልና ሲጀምር ሠርዐ ሰንበተ ለሰብእ እረፍተ ይጀምራልና አራተኛዋ ሰንበት ሠርዐ ሰንበተ ለሰብእ እረፍተ ትባላለች። አንድም ሰንበት ለሁሉም ፍጥረት ዕረፍት ሆና እንደተሰጠች ሲናገር ስያሜውን ሠርዐ

ሰንበተ ለሰብእ እረፍተ ተብሏል፡፡ "ሠርዐ ሰንበተ ለዕረፍተ ዚአነ" እንዲል መጽሐፈ ኪዳን፡፡

❖ ሳምንታቱን በዚህ መልክ የከፋፈለውም ሊቁ ቅዱስ ያሬድ ነው ድጓ ዘአስተምህሮ፡፡ ከመጀመሪያው ሳምንት ከአስተምሕሮ በቀር የአራቱ እሑዶቹ ስያሜ ከዐቢይ ጾም ሰንበታት ጋር አንድ ዓይነት ነው፡፡

## የሰንበታቱ ስያሜ ከዐቢይ ጾም ጋር ተመሳሳይ ነውን?

❖ የዘመነ አስተምህሮ ሰንበታት (እሑዶች) ስያሜ ከዐቢይ ጾም ሰንበታት ስያሜ ጋር ተመሳሳይ ይሁን እንጂ በእነዚህ ሳምንታት ሌሊት የሚዘመሩ መዝሙራት፣ በቅዳሴ ጊዜ የሚነበቡ ምንባባትና የሚቀርቡ ትምህርቶች ግን በይዘትና በምሥጢር ይለያያሉ፡፡ ትምህርቶቹ በምስጢር ይለያያሉ ስንልም በዚህ ወቅት የሚነገረው ምሥጢርና ይዘት በወቅቱ ላይ የሚያተኩር መሆኑን ለመግለጽ ነው እንጂ በየትኛውም ጊዜ በቤተክርስቲያናችን የሚቀርበው ትምህርት አንዱ የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው፡፡

❖ ዘመነ አስተምህሮ እንዳለቀ ዘመነ ስብከት ይገባል፡፡ ይህም ከታህሳስ 7 እስከ ታህሳስ 26 ቀን ያለው ዘመን ዘመነ ስብከት ይባላል፡፡ ዘመነ ስብከት የተባለበት ምክንያትም ነቢያት የጌታን በሥጋ መምጣት አምልተውና አስፍተው በትንቢትና በትምህርት መስበካቸውን ቤተክርስቲያን እያሰበች ሰውን ለማዳን ወደ ምድር የመጣውን አምላክ የምትሰብክበት ወቅት በመሆኑ ነው፡፡ በዘመነ ስብከት የሚገኙ ሰንበታት፦

## 1. ስብከት

❖ በዚህ ሰንበት በኦሪተ ሙሴ፣ በነቢያትና በመዝሙራት አስቀድሞ ስለ ክርስቶስ ሥጋን ተዋሕዶ ሰው መሆን ትንቢት ተነገሮ፣ ምሳሌ ተመስሎ፣ ሱባዔ ተቆጥሮ እንደነበር ይነገራል፤ ይሰበካልም፡፡ ስለዚህ ነቢያቱ አስቀድመው መምጣቱን ሰብከው ስለነበር ያንን ለማሰብ ይህ ሰንበት "ስብከት" ተባለ፡፡ ስብከት ማለት ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር የሚያገናኝ ትምህርት ማለት ሲሆን በዚህ ሳምንት ከልደተ አብርሃም እስከ ልደተ ዳዊት ባለው ትውልድ ወስጥ ስለ ክርስቶስ ሰው መሆን የተሰበከው ስብከት ይታሰባል፡፡ የነቢያት ስብከት በስብከት ሰንበት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሙሴ በሕግ ነቢያትም በትንቢት እንደጻፉለት የሚናገረው ወንጌል ይነበባል ዮሐ 1÷44፡፡ ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊትም "እጅህን ከአርያም ላክ አድነኝም" መዝ 143÷7 በማለት ስለ ክርስቶስ ማዳን በትንቢት መነጽር ተመልክቶ የዘመረው የመዝሙር ክፍል እንዲሁ ይሰበካል፡፡ ከዐበይት ነቢያት አንዱ የሆነው ነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይያስም "ሰማዮችን ቀድደህ ምነው ብትወርድ! ተራሮችም ምነው ቢናወጡ" ኢሳ 64÷1 ብሎ ስለክርስቶስ ከሰማየ ሰማያት መውረድ፣ ከድንግል ማርያምም መወለድ የተናገረውን ትንቢት ቤተክርስቲያን ትሰብካለች፡፡ የቤተክርስቲያናችን ስብከት ብርሃናተ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ በመልእክቱ "እኛስ የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን" 2ኛ ቆሮ 4፡5 እንዳለው ቤተክርስቲያን በተለይ በዘመነ ስብከት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጆች የሰጠውንና የፈጸመውን የማዳን ተስፋ ትሰብካለች፡፡ ቤተክርስቲያናችን መቼም ቢሆን መቼ፣ በጊዜውም አለጊዜውም፣ ሲሞላም

ሲያጎድልም ስለ ኃጢአታችን የሞተውንና አምላክ ወልደ አምላክ የሆነውን ክርስቶስን ትሰብካለች፡፡

## 2. ብርሀን

❖ የዘመነ ስብከት ሁለተኛው ሰንበት "ብርሀን" ይባላል፡፡ ነቢያት የነፍሳችን ብርሀን ይወለዳል ብለው ስለመስበካቸው፣ እውነተኛ ብርሀን ይመጣል ብለው ስለማስተማራቸው የሚታሰብበት ሲሆን በዚሁ ኢየሱስ ክርስቶስ አማናዊ ብርሀን መሆኑ ይሰበካል፤ ይዘመራልም፡፡ ከዚሁ ጋር ዘመነ ብሉይ መከራ ሥጋ፣ መከራ ነፍስ የጸናበት የሰው ልጅ ብርሃን ከሆነው አምላክ ጋር የተራራቀበት ስለነበር ነቢያት ያሉበትን ያን ዘመን ጨለማ ብለው በመግለጥ የነፍሳችን ብርሀን ይወለዳል፣ እውነተኛ ብርሃን ይመጣል ብለው ስለመስበካቸው የሚታሰብበት ቀን ወይም ሳምንት ነው፡፡ በዚህ ሳምንት ከልደተ ዳዊት እስከ ፍልሰተ ባቢሎን የነበረው 14 ትውልድ ይታሰብበታል፡፡ የነቢያት ጸሎት ነቢያት የአምላክን ማዳን ከጠበቁባቸውና፣ ከገለጡባቸው መንገዶች አንዱ ብርሃን ነው፡፡ ልበ አምላክ ክቡር ዳዊትም ወደ ትክክለኛው መንገድ የሚመራ ብርሃን ወደ ዓለም እንዲመጣ "ብርሃንህንና ጽድቅህን ላክ" መዝ 42÷3 እንዲህ ብሎ ይጸልይ ነበረ፡፡ ይህም ብርሃን፣ ጽድቅ፣ እውነት የሆነውን ልጅህን ወልድን ላክልን፤ እርሱ መርቶ ወደ መንግሥተ ሰማያት ያስገባን ዘንድ ማለት ነው፡፡ እውነተኛው ብርሀን ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ "ለሰው ሁሉ የሚያበራው እውነተኛው ብርሃን ወደ ዓለም መጣ" ብሎ እንደመሰከረው እውነተኛ ብርሀን ስለሆነው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ብርሀንነት የሚሰበክበት ሰንበት ነው፡፡ ዮሐ 1÷1-14፡፡ ጌታችንም በመዋዕለ ስብከቱ "እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፤ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም" ዮሐ 8÷12 ብሎ እንዳስተማረው በዚህ ሰንበት ስለ እርሱ ብርሀንነትና ክርስቲያኖችም እርሱን ብርሀናቸው እንዲያደርጉት ይሰበካል፡፡ የሕይወታችን ብርሀን በዚህ ዕለት "ከብርሀን የተገኘ ብርሀን" የተባለ ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ ብርሃን መሆኑ ይሰበካል፡፡ "ብርሃን ወደ ዓለም መጣ" እየተባለ በቅዱስ ያሬድ መዝሙር ይመሰገናል፡፡ እኛም አባቶቻችንን አብነት አድርገን ቅዱስ ኤፍሬምም በሰኞ ውዳሴ ማርያም እንዳስተማረን "ብርሃን ዘበአማን ዘያበርህ ለኵሉ ሰብእ ለእለ ይነብሩ ውስተ ዓለም ፡፡ በእንተ ፍቅረ ሰብእ መጻእከ ውስተ ዓለም ፡፡ ወኵሉ ፍጥረት ተፈሥሐ በምጽአትከ ፡፡ እስመ አድኃንኮ ለአዳም እምስሕተት ወረሰይካ ለሔዋን እግዓዚተ እምፃዕረ ሞት ፡፡ ወወሀብከነ መንፈሰ ልደት ፡፡ ባረክናከ ምስለ መላእክቲከ፡፡ ሰአሊ ለነ ቅድስት፡፡" በማለት የሕይወታችን ብርሀን የሆነውን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እናመሰግናለን፡፡

## 3. ኖላዊ

❖ የዘመነ ስብከት ሦስተኛው ሰንበት " ኖላዊ" ይባላል፡፡ ኖላዊ ማለት እረኛ ወይም ጠባቂ ማለት ሲሆን በዚህ ዕለት ነቢያት የእግዚአብሔር ልጅ እውነተኛ ጠባቂ ሆኖ ይገለጣል ብለው መተንበያቸው እና ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ ጠባቂ መሆኑ ቤተክርስቲያናችን እያሰበች የምትዘምርበት፣ የምትቀድስበት፣ የምታመሰግንበት ዕለት ነው፡፡ የእስራኤል ጠባቂ: ነቢያት ራሳቸውንና ሕዝበ እስራኤልን ብሎም

ዓለምን እረኞቻው እንደተዋቸው በጎች በመቁጠር ስለ እውነተኛው እረኛ መምጣት ትንቢት ተናግረዋል፡፡ በዚህ ሰንበት ከፍልሰተ ባቢሎን እስከ ልደተ ክርስቶስ ድረስ ያለው አሥራ አራት ትውልድ የነበረው ሰንበት ይታሰባል፡፡ በዚህ ሰንበት ቤተክርስቲያናችን እረኛ የሌለው በግ ተኵላ ነጣቂ እንዲበረታበት በበደሉ ምክንያት ከትጉህ እረኛው የተለየው የሰው ልጅም ሰብሳቢና የሚያሰማራ ጠባቂ እንዲኖረው ነቢያት ዮሴፍን እንደ መንጋ የምትመራ በኪሩቤል ላይ የምትቀመጥ የእስራኤል ጠባቂ ሆይ አድምጥ በማለት ይማፀኑ እንደነበር ታስተምራለች፡፡ ቸር ጠባቂ የትንቢቱ ፍጻሜ ሲደርስ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "መልካም እረኛ እኔ ነኝ፤ መልካም እረኛ ነፍሱን ስለ በጎቹ ያኖራል" ዮሐ10÷11 በማለት እውነተኛ እረኛ እርሱ መሆኑን መልስ ሰጥቷል፡፡ ስለራሱም መልካም እረኛ እኔ ነኝ አብም እንደሚያውቀኝ እኔም አብን እንደማውቀው የራሴን በጎች አውቃለሁ የራሴም በጎች ያውቁኛል፤ ነፍሴንም ስለ በጎች አኖራለሁ፡፡ ዮሐ 10÷15 በማለት አስተምሯል፡፡ በልበ አምላክ ክቡር ዳዊትም "እግዚአብሔር እረኛዬ ነው የሚያሳጣኝ የለም በለመለመ መስክ ያሳድረኛል" መዝ 22÷1 ተብሎ እንደተጻፈ በዚህ የጾም ወቅት አቤቱ ብርሀንህንና ጽድቅህን ላክ ቸሩ እረኛችን ሆይ ተቅበዝብዘናልና እባክህ አስበን፣ የቀዘቀዘው ፍቅራችንን መልስልን፣ አንተ እውነተኛ ሰላምህን ስጠን እያልን ምንም ወደ ማያሳጣን ወደ እውነተኛው እረኛችን ወደ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በንስሐ ልንመለስ ይገባል፡፡ ከተኩላዎች ተጠበቁ ለክርስቲያኖች ሁሉ የታመነ ጠባቂ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ በተጨማሪም በጎቼን ጠብቅ ብሎ ቅዱስ በጴጥሮስ በኩል አደራ የተሰጣቸው ካህናተ ቤተክርስቲያን የመንጋው ጠባቂ ናቸው፡፡ ነገር ግን በዚህ ሐሰተኛ በበዛበት ዘመን እውነተኞቹን እረኞች ከተኩላዎቹ መለየት ያስፈልጋል፡፡ የምንለያቸውም በፍሬያቸው ነው ማቴ 7÷15፡፡ መልካም ዛፍ መልካም ፍሬ እንዲያፈራ መልካም እረኛም ለበጎቹ መልካምን ያደርጋል፡፡ ተኩላ ግን በጎችን ሊጠብቅ ሳይሆን ሊነጥቅ እንደሚመጣ ሐሰተኞች እረኞችም ምዕመናንን ሊጠብቋቸው ሳይሆን ሊነጥቋቸው ይፍጨረጨራሉ፡፡ ነገር ግን መጨረሻቸው ጥፋት ስለሆነ ልናውቅባቸው ይገባል፡፡

- ❖ በአጠቃላይ በዚህ በገና ጾም ነቢያትም ሐዋርያትም ጾመው በረከት አግኝተውበታል፡፡ እኛ ምእመናንም እንደ እነርሱ በረከትን እናገኝ ዘንድ ይህንን ጾም መጾም እንደሚገባን የቤተክርስቲያን አባቶች ሥርዓት ሠርተውልናል፡፡ በዚህም መሠረት የነቢያት፣ የሐዋርያት፣ የጻድቃንና የሰማዕታት አምላክ ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም፣ ከቅዱሳን ነቢያትና ሐዋርያት በረከት እንዲያሳትፈን፤ መንግሥቱንም እንዲያወርሰን ሁላችንም በዚህ በጾመ ነቢያት ወቅት በጾም በጸሎት ተወስነን እግዚአብሔርን ልንማጸነው ይገባል፡፡

## ዋቢ መጻሕፍት


1. መጻሐፍ ቅዱስ
2. የመናገሻ ገነተ ጽጌ የሣልሳይ መማሪያ መጻሐፍ
3. ኆኅተ ስብከት ዘቅዱስ ያሬድ በሊቀ ጉባኤ ጌታሁን ደምጸ
4. አድማሱ ጀንበሬ ሕይወቱ ወሐተታ መጻሕፍቱ
5. መጽሐፈ ኪዳን ትርጓሜ